ለእርስዎ ልናደርግልዎ ፈቃደኛ የሆንነው ነገር ይደንቅዎታል

ካረን ማካቢ ማህበር
(Keren Maccabi Association)

ይምጡና ለአባላቱ ደህንነት ከማካቢ የጤና እንክብካቤ አገልግሎት ጋር የሚሰራውን ከረን ማካቢን (ማካቢ ፈንድን) ይወቁ።

የከረን ማካቢ አባል መሆን በማካቢ የጤና እንክብካቤ አገልግሎት የማይሰጡ መጠነ ሰፊ የደህንነት አገልግሎቶችን ለማግኘት ያስችላል።

קרן מכבי

በማህበሩ የሚሰጡ ዋና ዋና አገልግሎቶች፡-

ለህክምና የገንዘብ እገዛ

ለህክምና ፍላጎቶቻቸው ለመክፈል የገንዘብ እገዛ የሚያስፈልጋቸው አባላት በእርዳታ እና / ወይም ከኢንዴክስ ጋር በተገናኙ ከወለድ ነጻ ብድሮች ያገኛሉ። በየአመቱ ገንዘቡ/ፈንዱ በህክምና ወጪ፣ በህክምና መሳሪያዎች፣ በጥርስ ማስተካከል ህክምና፣ በህጻናት እድገት ህክምና፣ የስነልቦና ህክምና፣ የኦቲዝምና የሰውነት ((ሶማቲክ)ችግሮች ከህክምና ጋር ተዛማጅ ለሆኑ ችግሮች እና ለመሳሰሉት በሺዎች የሚቆጠሩትን አባላት ያግዛል።

በማህበረሰቡ ውስጥ ማህበራዊ ተሳትፎ

ካረን ማካቢ፣ የማካቢ የጤና እንክብካቤ አገልግሎትን በደህንነትና በማህበራዊ ተሳትፎ እንቅስቃሴዎች የሚያግዘው ሲሆን በተጨማሪም የማህበረሰብ በጎ ፈቃድ ፕሮግራሞች ላይ በጎ ፈቃደኝነትን ያስተዋውቃል።

ከፈንዱ የቅርብ ጊዜ እንቅስቃሴዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል፡-

ማንበብን የሚያበረታታውን የንባብ ጥሪ (Call to Reading) ፕሮጀክት ማገዝ

በህጻናት ሀኪሞች የተዘጋጁ መጻህፍት በዋርም ዊንድ (Warm Wind) ፕሮጅክት ላይ እንቅስቃሴዎችን በማዘጋጀት መርዳት

ከዘር ማጥፋት ጭፍጨፋው (Holocaust) ለተረፉት ባህልና መንፈስ (ከኢሼል ማህበር እና የአረጋዊያን ዜጎች ሚኒስቴር ጋር በመተባበር)

ለአባላት የሚሰጡ ብድሮች

እኛ በካረን ማካቢ የምንገኝ ያልተጠበቁ የህክምና ወጪዎች በእለት ተእለት ኑሮ ላይ እንዲሁም በገንዘብ አባላቶቻችን ላይ ችግሮችን ሊያስከትሉ እንደሚችሉ እንረዳለን። ስለዚህም ለፈንዱ አባላት ከኢንዴክሱ ጋር የሚገናኙ ለህክምና ወጪ የሚሆኑ ብድሮችን እናመቻቻለን። የሚሰጠው ብድር ከጊዜ ወደ ጊዜ በፈንዱ የብድር ኮሚቴ በሚሰጠው የጣሪያ ገደብ ላይ የተመሰረተ ነው።

ለህክምና ተማሪዎችና ከህክምና ጋር ተዛማጅ ለሆኑ ሙያዎች ለሚማሩ ተማሪዎች ስኮላርሺፕ

ካረን ማካቢ የሚቀጥለውን የህክምና ባለሞያዎችና ቴራፒስቶችን ማጠናከርን ግቡ አድርጎ ይንቀሳቀሳል። ለዚህ አላማ ፈንዱ እድሜያቸው ከ29 አመት በታች ለሆኑና ህክምና ወይም በፈንዱ ስኮላርሺፕ ኮሚቴ የጸደቁ ከህክምና ጋር ተዛማጅ ለሆኑ ሙያዎች ለሚማሩ ተማሪዎች ስኮላርሺፕ ይሰጣል። በየአመቱ ለተማሪዎች በመቶዎች የሚቆጠሩ ስኮላርሺፖች ይሰጣሉ። የሚሰጡትን ስኮላርሺፖች የሚጸድቀው ስኮላርሺፕ የማግኛ መስፈርቶችን በሚያዘጋጀውና በየአመቱ ከማመልከቻ ቀን አስቀድሞ በሚያስታውቀው የስኮላርሺፕ ኮሚቴ ነው።

ማካቢ ወጣቶች (Maccabi Youth) – የወደፊቱን ትውልድ መገንባት

ካረን ማካቢ፣ የማካቢ ወጣቶች እንቅስቃሴዎችን በገንዘብ ለመደገፍ ይሰራል። ይህ እስከ 1200 የሚደርሱ ወጣቶች በደርዘን በሚቆጠሩ የማካቢ የጤና እንክብካቤ አገልግሎት ቅርንጫፍ መስሪያ ቤቶችና ጽ/ቤቶች ውስጥ የሚያጠኑበትና የበጎ ፈቃድ ስራ የሚሰሩበት ፕሮግራም ነው። ፕሮግራሙ ከህክምና ጋር ተዛማጅ በሆኑ ዘርፎች ላይ ለወጣቶች ያለክፍያ በሚሰጡ ኮርሶች የተውጣጣ ነው። የማካቢ ወጣቶች የበጎ ፈቃደኝነትንና ለማህበረሰብ አስተዋጾኦ የማድረግ ተሞክሮ ይኖራቸዋል እንዲሁም በእስራኤል ውስጥ ጤናማ የሆነ አኗኗር በመምራት አስተዋጽኦ ያደርጋሉ። ፕሮጀክቱ በአገሪቱ የተለያዩ ክፍሎች ላሉ ችግረኛ ለሆኑ ህጻናት መጽሃፍትን ማንበብና በወጣቶች መካከል ማንበብንና የባህል እንቅስቃሴዎችን ማበረታታትን ያካተተ ነው። ፕሮጀክቱ መጻሕፍት ማንበብን የሚያበረታታ ሲሆን ማንበብና መማር ከህጻናት ጤና ጋር ያለውን ግንኙነት አጉልቶ ያሳያል።

קרן מכבי

የካረን ማካቢ አባላት የሆኑትን 1,600,000 ዋስትና ያላቸውን አባላት ይቀላቀሉ

ለአባላት ጥቅም ወደሆኑት የደህንነትና የእገዛ እንቅስቃሴዎች በመምጣት አጋራችን ይሁኑ።

በካረን ማካቢ አባል መሆን አባላት በደንቡ ውስጥ የተዘረዘሩት አገልግሎቶች ተጠቃሚ ያደርጋቸዋል።

ካረን ማካቢ በጥሩና በመጥፎ ጊዜያት የሚያግዝዎ እውነተኛ ቤትዎ ሲሆን ከአባላቱ ደህንነት ጋር ተዛማጅ በሆኑ ጉዳዮች በሙሉ ከማካቢ የጤና እንክብካቤ ማዕከል ጋር አብሮ ይሰራል።

የማህበሩን አገልግሎቶችና እንቅስቃሴዎች ሙሉ በሙሉ ተጠቃሚ የሆኑትን አሁን ያሉትን 1,600,000 የፈንድ አባላት ለማገዝ፣ ለመታገዝና ቤትዎ እንዳሉ እንዲሰማዎ ይቀላቀሉ።

በፈንዱ አባል መሆን ግዴታ አይደለም - በምርጫ የሚደረግ ሲሆን በማካቢ የጤና እንክብካቤ አገልግሎት ወይም በተጨማሪ የህክምና አገልግሎቶች (Shaban) አባል ከመሆን ጋር የተለያዩ ናቸው
ከላይ የተጠቀሱት አንዳንዶቹ አገልግሎቶችም በድረ ገጹ ላይ በተጠቀሰው መሰረት በመጠባበቂያ ጊዜ ሁኔታ ላይ የተመረኮዙ ናቸው።
የፈንዱ አባል ለመሆን የሚከፈለው ገንዘብ እድሜያቸው 19 እና ከዚያ በላይ ለሆኑ አዋቂዎች በ4/2014 በተስተካከለውና ከኢንዴክሱ ጋር በተያያዘው መሰረት በወር 0.72 NIS ነው።

ለተጨማሪ መረጃ፣ እባክዎ በሚከተለው አድራሻ ድረ ገጹን ይጎብኙ፣ www.keren-maccabi.co.il

Keren Maccabi, 2 Kaufman Street (Textile House), Tel Aviv 68012
ስልክ: 03.7463150፣ ፋክስ: 03.7463156 Email: pniot_kerenmaccabi@mac.org.il